# ★ ዴሞክራሲያ ★

ዴሞክራሲያ ቅጽ 35 ቁጥር 5 ሚያዚያ 2002 ዓ.ም.

## ሚያዝያ 1964--ሚያዝያ 2002

## 38 የትግል ዓመታት

የሕዝብ የረጅም ዓመታት ትግልና ሰቃይ፣ ምኞትና ተስፋ በሚያዝያ 1964 ዓ.ም ለኢሕአፓ ምሥረታ ምክንያት ሆኗል። በቁጥር ትንሽ የሆኑ ወጣቶች ግን የሚሊዮኖችን የነፃነትና መብት ፍላጎት ያቀፉ ግዙፎች የሕዝብ ትግል መሪ ድርጅት እንደሚያስፈልገው በመረዳት ለተወሰኑ ዓመታት ድርጅታዊ ዝግጅቶችን ሲያደርጉ ቆይተው በሚያዝያ 1964 ኢሕአፓን ሊመሠርቱ በቅተዋል። በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ የመጀመሪያው ዘመናዊና ሕዝባዊ የፖለቲካ ፓርቲ/ድርጅት የሆነው ኢሕአፓ የተጣለበትን አደራና የገባውን ቃል ኪዳን ሚዛንና ክብደት ከመጀመሪያውም ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። ለ38 ዓመታት ብዙ መከራን ችሎ፣ የፋሺስቶችንና የጠባቦችን አረመኔ ጥቃት ተቋቁሞ፣ አያሌ ሻጥሮችን ተወጥቶ፣ የከሀዲና አንጃን ሻጥር በጣጥሶ ኢሕአፓ ዛሬም በትግል ሜዳ መገኘቱ፣ መቀጠሉ ለወደቁት ሰማዕታትና ለጭቁኑ ሕዝብ ሁሉ የሚያኮራ ነው።

ኢሕአፓ ሲመሠረት በሀገራችን የነበሩ ግዙፍ ችግሮችን በሚገባ ተንትኖና አውቆ በመራራ ትግል መሠረታዊ መፍትሔ የሚሆነውን ዴሞክራሲ ለማስፈን ወስኖ ነው። ከሰማንያ አምስት በመቶ በላይ የሆነውን ሕዝብ በገባርነትና ጢሰኝነት ቀይዶ ፍዳ ያሳይ የነበረውንና በፈላጭ ቆራጭ አፄ ይመራ የነበረውን ፊውዳል ሥርዓት ማስወገድና በቦታው ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ ማቋቋም ዋናው ተልዕኮ ነበር። በመሆኑም መሬት ለአራሹ የሚለው ዋና መፈክር የወጣቶች የትግል አርማ ሆኖ ተስተጋባ። አርሶ አደሩ ወይም ይባል እንደነበረው ጢሰኛውና ገባሩ የመሬቱና የላቡ ውጤት ባለቤት ይሆን ዘንድ የተስተጋባው ይህ መፈክር አሁንም ወቅታዊ ሆኖ ከመገኘቱ ሌላ ዛሬም ቢሆን የሰፊውን ሕዝብ ባለ መብትነትን የሚፃረሩ ክፍሎችን ሲያንቀጠቅጥና ሲያስጓራ የሚገኝ ነው። ይህ የመሬት ለአራሹ መፈክር (መሬት ላራሹ ነፍጥ ለተኳሹ እንዲሉ ጥንትም) የሥርዓቱን ማገርና ምሰሶ የነቀነቀ በመሆኑ አገዛዙም ተማሪዎችን በማጥቃትና ጥያቄውም ከቶ እንዳይነሳ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቶ ነበር። የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ዛሬም ምላሽ አልባ በመሆኑ አገዛዙ አርሶ አደሩ ከብሯል፣ ይኸው

በግና ሜዳሊያም እየተሸለመ ነው፤ የእጅ ስልክም ባለቤት ሆኗል እያለ ቢለፍፍም የብዙኀኑ አርሶ አደር ስቃይና መከራ፤ መበዝበዝና መሬት መቀማት፤ ድህነትና መራብ ግን የማይደበቅ ምፀት ሆኖ በመቀጠል ላይ ነው።

ተማሪና ወጣቱም በእነ መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥቱ ጊዜ የተጀመረውን የሥር ነቀል ለውጥ ፍለጋ አዝማሚያ በዚያው አጠናክሮ ከአፄው ሥርዓት ጋር ተቆራረጠ። ወጣቶች ዕጣቸውን የነገ ራዕያቸውን÷ ተስፋቸውን ከጭቁኑ ሕዝብ ካቆራኙም በኋላ ወደኋላ የሚመለሱ አልሆኑም። የተማሪዎች ቀጣይ ትግል ግን በራሱ የሕዝብን ትግል ወደ መምራቱ ደረጃ ሊሸጋገር ባለመቻሉና የፖለቲካ ድርጅትን ሚና የሕዝብ የሞያ ድርጅት ሊተካም ስለማይችል ወደ ቀጣዩ የትግል ደረጃ መሄዱ አስፈላጊ ሆኖ ወደ ድርጅት ምሥረታ መሸጋገር ዋና ጥያቄና ተግባር ሆነ። ይህ ሂደት ግን ውጣ ውረድ አልባ አልነበረም። በተማሪው ትግል ጊዜ ጃንሆይ/አፄው ምን አጠፉ፤ ሕዝቡ ነው አላዋቂና ጥፋተኛ የሚሉ እንድነበሩ ሁሉ (ከነዚህ ውስጥ በኋላ ብዙዎቹ የደርግ ጋሻ ጃግሬና የላቁ አብዮታውያንና ማርክሳውያን ነን ሲሉም ለመታዘብ በቅተን ነበር!) ድርጅት መመሥረት ጥያቄ ሲነሳም ሕዝብ አልነቃም፤ ለትግል አልተዘጋጀም፤ ለመደራጀትና የቁርጥ ቀን ትግል ለመጀመር ቢያንስ ገና ሁለት ትውልድ ይፈጃል የሚሉ ነበሩ (ከእነዚህም ብዙዎቹ የደርጉ አጋር ባንዳዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ ዛሬም የወያኔ ተለጣፊ ሆነው ይገኛሉ)። ድርጅት መመሥረት ዛሬ በኋላ መብራት ሲታይ ግልፅና ቀላል ቢመስልም በወቅቱ ግን አስቸጋሪና ውስብስብ ከመሆኑ ሌላ ሞካሪዎቹንም ያስወገዘ ነበር። ለድርጅት ምሥረታ ማለትም ለኢሕአፓ ህልውና መከሰት የመጀመሪያውንና የመሥራች ሚናውን የተጫወቱት በርካታዎቹ ዛሬ በህይወት ባይኖሩም ወይም ለእስር ተዳርገው ደብዛቸው ቢጠፋም የኢሕአፓ ምሥረታ ሂደት ምን ያህል ጥረትና ቆራጥነትን እንደጠየቀ የምንስተው አይደለም።

ኢሕአፓ የኢትዮጵያን ግዙፍ ችግሮች በፊት ለፊት አጢኖ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ሲነሳም መሠረታዊ የዴሞክራሲና የእኩልነት ጥያቄን በዝምታ ሊያልፍ የሚችል አልነበረም። ዛሬ አንዳንድ የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂዎች እንደሚሉት ሳይሆን እነዚህ ችግሮች በነበረው ሥርዓት የተቀፈቀፉና የተባባሱ ችግሮች ነበሩ። በኤርትራ የነበረውን ችግር ለምሳሌ ኢሕአፓም ወጣቱም የፈጠረው ሳይሆን የአፄው ሥርዓት የወለደውና በአብዛኛውም ከፌዴረሽኑ (መፍረስ) ጋር የተያያዘም መሆኑ የሚታወቅ ነው። የኤርትራው የመጀመሪያ ግንባር (ጀብሀ) የተባለው ሲመሠረትና ውጊያ ሲጀምር (በ1960 ዓ.ም.) ኢሕአፓ ገና አልተመሠረተም ነበር። የባሌና አጋዴን ውጊያዎችም ሆኑ የነጄኔራል ታደሰ ብሩና ማሞ መዘምር እንቅስቃሴ ክስተት ከኢሕአፓ መፈጠር በፊት ነበር። ለነዚህ ሁሉ ችግሮች ተጠያቂው ሥርዓቱ መሆኑ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። ኢሕአፓም ሲመሠረት እነዚህን ግዙፍ ችግሮች በተለይም የሕዝብ እኩልነትን ጥያቄ በሚመለከት መፍትሔ መሻትና ማቅረብ ነበረበትና የተደፋፈነው ችግር እንዲጋለጥ--ያበጠው እንዲፈነዳ--ና መፍትሔም እንዲፈለግ

ግንባር ቀደም ሆኖ መንቀሳቀስ ነበረበት፡፡ በሰጎን ፖለቲካ አላየሁም አልሰማሁም ብሎ እሪ የሚለውን የእኩልነት እጦት ጆሮ ዳባ ልበስ በሚል ማለፍ ሚናው ባለመሆኑም የሕዝብን እኩልነት በተመለከተ የራስን ዕድል መወሰንና በዴሞክራሲ እኩልነትን ማረጋገጥ አስፈላጊነቱን መግለፅ ማስተማርና በዚህም መንገድ አንድነትን በአዲስና በዴሞክራሲ መሠረት ላይ ለመገንባት ተነሳሳ፤ ጣረ፡፡ በዚህ መፍትኄ ፍለጋም ኢሕአፓ በነበረው ርዕዮትና አመለካከት መሠረት ምናልባትም ለጠባቦች አደጋ ሙሉ ግንዛቤን ያልያዘ ቢመስልም ከ1967 ጀምሮ ከጠባቡ ወያኔ ጋር ያካሄደው ትግልና ፍልሚያ ለፀረ ጠባብነቱና ለአንድነት ፈላጊነቱና ቀናዒነቱ በቂ ምስክር ነው፡፡ በኢሕአፓም ውስጥና ዙሪያ የሀገራችን ዜጎች ሃይማኖትና ብሔረሰብ ሳይለዩ መሰለፋቸውና መሰዋታቸውም የዚሁ አቅዋሙ ዴሞክራሲያዊነትና ትክክለኛነት ማጠየቂያ ነው ብንል ስህተት አይሆንም፡፡

ኢሕአፓ ሲመሰረት የፖለቲካ ፓርቲ ለሀገራችን ገና እንግዳ የነበረበት፤ የትግል ተመክሮ ያልዳበረበት፤ ሁሉም ነገር ሀ ሁ ተብሎ የሚሠራበት ሁኔታ እንደነበርም ማስታወስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ኢሕአፓ በሚያዝያ 1964 ቢመሠረትም፤ ከተመሠረተ ጀምሮም ህቡዓዊ ድርጅታዊ ሥራን በኢትዮጵያ ቢያጧጥፍም፤ የየካቲት አብዮት በ1966 ሲፈነዳ ድርጅቱ የመሪነት ሚናን ተረክቦ ትግሉን ወደ ድል ለመውሰድ በቂ አቅም አልነበረውም፡፡ ሆኖም የየካቲት አብዮት በ"ጊዜ እንስጥ" አቀንቃኞችና በጥገና ለውጥ አባወራዎች እንዳይደናቀፍ የበኩሉን አስተዋፅዖ በማድረግ የአቄውን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መንኮታኮት ከሕዝብ ጋር ሆኖ እውን ሊያደርግ ችሏል፡፡ ዛሬ ታሪካቸውን የረሱና ወይም የነበረውን ግፍ የሚክዱና የማያውቁ ክፍሎች ያን ዘመንና አቄውን ሊያቆነጁ ቢሞክሩም ገፈት ቀማሹ ሰፊው ሕዝብ ግን ያ ሥርዓት ምን ያህል ግፈኛ እንደነበር የሚረሳ አይደለም፡፡ 'ትኩሱ ሬሳ ደረቁን አስረሳ' ሆኖ ተኪዎቹ እየባሱ ያለፈውን ሥርዓት መራራነት ሊያዘናጉ ቢጥሩም ኢሕአፓ በበኩሉ ያን ፀረ ሕዝብ ሥርዓት ታግሎ ለውድቀት ማብቃቱን ይኮራበታል እንጂ የሚፀፀትበት አይደለም፡፡ የየካቲት አብዮት ሕዝባዊ ይዘትና ገፅታን በሕዝቡ የጋራ ተሳትፎ፤ በተነሱት የዴሞክራሲ ጥያቄዎች፤ የሕዝብ እኩልነት በጋራ በመጠየቁ፤ እስላም ክርስቲያኑ፤ ወጣት አዛውንቱ፤ ሴቱ ወንዱ ሁሉ በመሰለፉና በመቃወሙ የተረጋገጠ ነው፡፡ በመሆኑም ኢሕአፓ የተመሠረተባቸው መርሆች ሕዝባዊ መሆናቸው ሊታይ በቅቷል፡፡ የኢሕአፓም ሕዝባዊነት በዚሁ ዕውን ሆኖ ሥልጣን ከሕዝብ የቀማውን ደርግንም መታገል ባስፈለገበት ጊዜ ከፅንፍ እስከ አፅናፍ ተከስቶ በፖለቲካው መስክ ለፋሺስቶቹ መኮንኖች ሽንፈትን አከናንቧል፡፡

ኢሕአፓ ሲመሠረትና ኋላም ባወጣው የፖለቲካ መርህ ግብር ወይም ፕሮግራም እንዳሰፈረው የሰላማዊ ትግል መድረክ ከተከፈተና ካልተዘጋ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ሊታገል ዝግጁ መሆኑን ገልፆ ነበር፡፡ ይህን መንገድ ግን ደርጉም ሆነ ዛሬ ወያኔ ዘግተውና ከርችመው በመገኘታቸውና የህግ የበላይነት በመውደሙ ሌላ አማራጮችን መፈለግ የግድ ነበረ፤ ዛሬም ነው፡፡ በየካቲት የተከናወነውን ትግል ኢሕአፓ በወቅቱ ሲያቀርበው እንዲህ ብሎም እነደነበረ ማስታወስ ይጠቅማል፤

*"በየካቲት የተከናወነው ትግል:-*

- *የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከአገር አገር፤ ከዳር እዳር፤ ከአድማስ አድማስ በአንድነትና በአንድ ጊዜ የተነሳበት በመሆኑ፤*
- *የቀረቡት ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የተለያዩ ጭቁን መደቦችን ፍላጎትና ግብ የሚያስተጋቡ በመሆናቸው፤*
- *አርሶ አደሮች በተለያዩ ሥፍራዎች--በመቱ፤ በከፋ፤ በአርሲ ጨርጨርና ወበራ-- በመደብ ጠላቶቻቸው ላይ ጉዳት በማድረሳቸው፤ ላብአደሮችም ከፍተኛ የትግል ሚና የነበረውን የአራት ቀን የሥራ ማቆም አድማ በማድረጋቸውና፤*
- *የትግሉ ግለት ከቀን ወደቀን እያደገና እየጨመረ ሁሉን አድራሽ መሆኑ፤ ልዩና አዲስ የትግል ምዕራፍ ሆነ፡፡*

*<u>ሆኖም የሰፊውን ሕዝብ መፈክሮች የሚያቀናጅና ትግሉንም የሚያደራጅ መሪ ኃይል በመታጣቱ የመንግሥት ሥልጣን ከባለቤቱ ከሕዝብ እጅ ሳይገባ ቀረ</u> ፡፡" (ዴሞክራሲያ ቅፅ 2 ቁጥር 9 ሰኔ 3/1967 ዓ.ም.)*

**የሕዝብን ሥልጣን የቀማውን ቡድን፥ 'ሕዝብ ሞግዚት አያሻውም፤ ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም' ብሎ የታገለው ኢሕአፓ በፖለቲካው መስክ በደርግና በምሁር ደጋፊው ቡድኖች ላይ የበላይነትን በመያዙ የመኮንኖቹ ሕግ አልባ አገዛዝ በኢሕአፓና በሕዝብ ላይ ጦርነት ማወጅን መረጠ፡፡ የሕዝባችን ቁስል ገና ሳይመጥና ሳይደርቅ ዛሬም የታሪክን ብረዛ ሥራዬ ብለው የተያያዙት ዕቡዮች እንደሚሉት ሳይሆን በኢሕአፓና በሕዝብ ላይ በመጀመሪያ የአፈና ጅራፉን ያጮኸው ደርግ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በነአሊ ሙሳና ጌታቸው ሺበሺ የሚመሩ ነፍሰ ገዳዮች እየተዟዟሩ ስንቱን ሲገድሉ፤ የደርግ አጋር ምሁራን የሚገደሉ ብለው ስም ዝርዝር ሲያስገቡና ነበልባል ጦር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ሲደረግ፤ ተገድለው የተጣሉ በሰበታና ሌሎችም ቦታዎች መታየት ሲጀምሩ፤...ወዘተ ይህ ሁሉ ሲከሰት ኢሕአፓ አንድም የአፀፋ ተኩስ አለማሰማቱ ሐቅ ነው፡፡ በፖለቲካው መስክ ሽንፈት የደረሰበት አገዛዝ፤ የሕግን የበላይነት ማክብር የተሳነው ገዢ ቡድን፤ ያለኝ አማራጭ ማፈን መግደል ብሎ ሲነሳና መግደልም ሲጀምር ኢሕአፓ የራስ መከላከል እርምጃን ለመውሰድ ተገዷል፡፡ ለትኝን ልጓም የሚያጎርሱ የዚያ አገዛዝ ሎሌዎችና ዋሾዎች ዛሬ በተገላቢጦሽ ኢሕአፓ ተኩስ ከፈተ ወይም ደርጉ ተመልካች ሆኖ ሳለ ኢሕአፓና ከደርግ ያደሩት ምሁሮች ተጨራረሱ፤ አልፎም ደግሞ ኢሕአፓ ሰው አስጨረሰ የሚሉት ሁሉ መሰረተ ቢስነት በነበረው ሐቅ የሚጋለጥ ነው፡፡ ኢሕአፓ በከተሞች ያደረገውን የወቅቱ ትግል ማቆም በነበረበት ጊዜ ባለማቆሙ ራሱን ስህተተኛ ብሎ ከሃያ ዓመት በፊት የወቀሰ ቢሆንም ፋሺስቱን ደርግ በመታገሉና ፀረ ሕዝቦችን ባለው አቅም በመቅጣቱ ግን የሚቆጨው ነገር የለም፡፡ መስዋዕትነት አልባ ትግል የለምናም የእነ "አስጨረሰ"ን አሞት ቢስ ክስና የአዞ እንባን ከመጤፍ የሚቆጥረው አልሆነም፡፡**

የተቀማጭ ምላሱ ምላጭ መሆኑን ያውቃል። ለሀገራችንም ገና ለማለቅ ዝግጁ ነውና--እያለቀም ቆይቷልናም ነው።

አረመኔው ደርግ ኢሕአፓንና የመሳሰሉትን ሀገር ወዳድ ድርጅቶች በሽብር በማጥቃቱ ሜዳውን ለብሔርተኛ ድርጅቶች ሰጣቸውና እነሆ ሀገራችን ዛሬ ለምትገኝበት አስከፊ ሁኔታ መንገድ ጠረገ። ኢሕአፓ ከደርግ ቀይ ሽብርና ፍጅት በተጨማሪ በውስጡ የተነሱትን ርጋፊዎችንና አንጃዎችንም መቋቋም ነበረበት። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ጠባቦች ተባብረው በትግራይ (አሲምባ) ጦርነት ከፈቱበት፣ የአካባቢ ፀረ ኢትዮጵያ ሀገሮችና ሉዓላዊነቷን ተፃራሪ የሆኑ ኃያላን ጠባቦችን እየረዱ ተነሱበት። የኢሕአፓ ጠላቶች የበዙት የኢትዮጵያ ጠላቶች በመብዛታቸው ነው። ድርጅቱ መቸም ቢሆን መቼ፤ የመጣ ቢመጣ የሀገራችንን ጥቅም አሳልፎ ለባዕዳን ለመስጠት ዝግጁ ባለመሆኑ ጥርስ ተነከሰበት፤ ሀገር ሻጮች ግን ትላንትም ዛሬም ድጋፍ ሲያገኙ የምናየው ሐቅ ነው። ኢሕአፓና የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የተቆራኙ ሆነው ለ38 ዓመት መቆየታቸው ሊካድ የሚችል አይደለም። በመሆኑም ድርጅቱ መመኪያው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ የምዕራቡ ምዕዋት ባለመሆኑ ከሕዝብ ጋርና ከሕዝብ ጎን ሆኖ መጪውን ሁሉ ሲጋፈጥና መስዋዕትነትንም ሲከፍል ቆይቷል። በዚህም ይኮራል እንጂ አያዝንም፤ አይፀፀትም። ይቀጥልበታል እንጂ በትንሿ ቀውስም ሰማዩ እንደሚደፋባቸው ማረኝ ብሎ ከአረመኔ አገዛዝ ሆነ ከባዕድ ጫማ ስር አልተደፋም። ኢሕአፓ በትግል ሂደት የተሳሳተውን እያረመ፤ የጎደለውን እያሟላ፤ ቁስሉን እያከመና እየተጠናከረ እነሆ እስከዛሬ ትግሉን ለመቀጠል ችሏል። ይህ በራሱ በቀላሉ የማይገመት ፅናትና ችሎታ ከመሆኑ ባሻገር ኢሕአፓ ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን አክብሮ መታገሉም የቀጠለ ነው። በእርግጥ ከውስጡና ከመሃሉ ሙጃዎች እየበቀሉ፤ ሕዝብን እየካዱ፤ ለሕዝብ ጠላት እየተጎነበሱ ጉዳት ማድረሳቸውንም መጥቀስ የግድ ነው። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ ነው ችግሩ። ያም ሆነ ይህ ግን ኢሕአፓ ጠባቦችና ቅጥረኞቻቸው ቢረባረቡበትም ለተጠላ ጌታ ምስለኔ መሆን ልምዱ ባለመሆኑ ትግሉን ቀጥሏል።

በሚያዝያ 1964 ዓ.ም. ኢሕአፓ ሲመሠረት ኢትዮጵያ በክፉ አገዛዝ ሥር ፍዳ እያየች ያለች ሀገር ነበረች። ዛሬም አልቀረላትም፤ አልተለወጠላትም። በዚያን ወቅት ዋነኛ የትግል መፈክር የነበሩት "መሬት ለአራሹና፥ ዴሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ" ዛሬም ወቅታዊና የትግላችን መፈክሮች ናቸው። በሥልጣን ያለው ቡድን በጭቆና ካለፉት የባሰ እንጂ የሚተናነስ ካለመሆኑ ሌላ ይሁነኝ ብሎ ሕዝብን ለመከፋፈልና ሀገርን ለማዋረድ የተነሳ ቡድን ነው። ኢሕአፓ ከወያኔ ምሥረታ ጊዜ ጀምሮ ይህን ፀረ ኢትዮጵያ ኃይል በመታገል መስዋዕትነት የከፈለው የወያኔ ቡድን ሀገር አጥፊ እንደሚሆን በማወቁ ነው። የወያኔ የመነሻ መርሁ ግንጠላ በመሆኑ፤ በሕዝብ ላይ ጥላቻን ማሰራጨትና ኢትዮጵያዊነትን መካድ በመሆኑ ኢሕአፓ ገና ከጠዋቱ ታግሎታል። ወያኔ በባዕዳን እርዳታ ወደ ሥልጣን ሲገሰግስም በኢሕአፓ ብርቅዬ ልጆች ሬሳላይ ተረማምዶ መሆኑም ከዚሁ የተነሳ ነው።

ወያኔ በኃያል መንግሥት ድጋፍ ሥልጣን ሲይዝም ለወያኔም ለባዕዳንም በመጎንበስ፤ ለወያኔ ጊዜ እንስጠው በማለት፤ ሹመት ለመቀራመትና በሀገር ለመቀለድ በመነሳት ሕዝብን አልካደም--ሕዝብን ለፀረ ወያኔ ትግል ሊያደራጅ ተነሳ--ቀጠለ እንጂ። በዚህም ብዙ መስዋዕትነትን ከፍሏል። 'ጅብን ከምኑ መታኸው' ቢሉት 'ከአፉ' ቢል አሰፋህለት እንደተባለው፤ ወያኔን በባልቱም እያጀበ፤ ተለጣፊነትን አቀንቅኖ ለፀረ ሕዝቡ አገዛዝ በላተኛ አፍ ሀገርና ወገንን አቀባይ አልሆነም። በአጭሩ ሚያዝያ 1964 የገባውን ቃል ኪዳንና የሰማዕትን ደም አልረገጠም።

ብዙ ጋሬጣዎችን አልፎ ድርጅት መሥርቶ የሕዝብን ትግል ለማጠናከር መቻል ራሱ ከባድ ሥራ ቢሆንም በሚሰነዘሩት ጥቃቶች የተነሳ አለመክሰምም የሚደነቅ ችሎታ ነው። ስንት ድርጅት ፈልቶ እንደ ጠዋት ጤዛ ከመቅፅበት ሲከስም ማየት ተገደናልና የኢሕአፓን በፅናት መቀጠል--ያውም መርህን ለጥቅም ሳይቸበችብ--ስናይ ደግሞ ሕዝባዊ መርህን ያነገበና የሕዝብ ድጋፍን የሚያገኝ ድርጅት የሚጠፋ አለመሆኑን መረዳት እንችላለን። ኢሕአፓ ለሥልጣን አለመብቃቱ ሽንፈት የሚመስላቸውና በትግሉ ሂደት የተገኘውን ድል ማየት የተሳናቸው እንዳሉ ይታወቃል። ግን ገዢ ክፍሎች የማይፈልጉትን እንዲቀበሉ መገደዳቸው ራሱ የትግል ውጤት መሆኑ መረሳት የለበትም ብንል ትክክል ነው። የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት አፈቀላጤ፤ የሕዝብን መብት የቡርዥዋ የከበርቴ ነውና አፍናለሁ ሲል የነበር ደንጊ ቡድን በግድ በአፋዊ ደረጃ እንኳን አቅዋም መቀየር መገደዱ መታየት ያለበት ነው። እንደፈለጉትና እንዳቀዱት ወይም እንደቀድሞው ሊገዙ አለመቻላቸውም የሕዝብ ትግል ውጤት ነው። ይህ የተከማቸ ትግልና የተገኘ ድልም በ1997 ለወያኔ መቃብር ቆፍሮ ሊከተው ሲል--ዛሮች 'የጨረሰን የራሳችን ጠማማ ነው' እንዳሉት ሁሉ--ሕዝብን የከዱ ክፍሎች ለወያኔ ታዳጊ በመሆን እንደረዱት አይተናል። ከ200 በላይ ዜጋ ህይወቱ ሲጠፋ ብዙ ሺዎችም ለእስር ተዳርገዋል። ለሀገርና ለወገን ሲሉም "ተጨርሰዋል"፤ መከራንም እስካዘሬ እየተቀበሉ ናቸው። ትግሉ ልዩ መልኩ ሀገር አድን መሆኑ ነውና ከመቸውም ጊዜ በበለጠ 'ፈሪ ተለይ! ባንዳ ራቅ!' እምቢልታ መነፋቱ በጣም አስፈላጊ ነው። የሕዝብ ጎራ በባንዳ ጥርቃሞዎችና ለአፋቸው እንኳን ሕዝብን ይቅርታ ባልጠየቁ ነፍሰ ገዳዮች እንዳይጨቀይ ኢሕአፓ የዛሬ 38 ዓመት በገባው ቃል ኪዳን መሰረት ዘብ ቆሟል።

የሕዝብ ትግልን የድርጅት ፍላጎት አሟልቶ ከሕዝብ ጎን በመቆም 38 ዓመት ሙሉ የታገለውና አሁንም እየታገለ ያለው የጨቋኞችና የከሀዲዎች ማርከሻው ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ትግሉን በመቀጠል የሕዝብ ድልና አይቀሬ አቸናፊነት እስኪከሰት ድረስ ይዋደቃል።

ሕዝባዊ ቃል ኪዳናችን ክቡር ነው!
እንታገላለን፤ እናቸንፋለንም!!